# ከነገ በስቲያ ፓርላማው ስራ ይጀምራል

## ከመክፈቻው አንስቶ ም/ቤቱን ለማወክ ዕቅድ መኖሩ ተጠቆመ፤ ዋናዎቹ ተቃዋሚዎች ተቃውመውታል

ሶስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሁለተኛ ዓመት የስራ ዘመን ሰኞ መስከረም 29 ቀን 1999ዓ.ም በ8:30 ሰዓት በይፋ ይጀምራል:: ይህንኑ ምክንያት በማድረግና የመጭውን ስራ ዘመን ትኩረት አስመልክቶ የፓርላማው አፈ ጉባዔ የተከበሩ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ፣ በምክር ቤቱ የተቃዋሚውን ክፍል የሚመሩት የተከበሩ አቶ ልደቱ አያሌው፣ አቶ ተመስገን ዘውዴ እና ሌሎችም ባገባደድነው ሳምንት ውስጥ መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳል::

አፈ ጉባዔ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ከዚሁ አያይዘው ትላንት አርብ በሰጡት መግለጫ እንደገለፁት ምክር ቤቱን የሁሉም ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ይበልጥ ያረጋገጠ መድረክ ለማድረግ የተነደፉና በዚሁ የስራ ዘመን የሚተገበሩ እቅዶች አሉ:: በገዢውና ፓርላማው ውስጥ ወንበር ይዘው በሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በ1998ዓ.ም የተጀመረው የምክክርና የድርድር ባህልና መድረክ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፣ ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጉዳዮችም ለሁሉም ወገኖች አስማሚ በሆነ መልኩ እንዲቋጭ ጥረት እንደሚያደርጉ አፈ ጉባዔውን ጨምሮ የሁሉም ወኪሎች አዎንታዊ ተስፋቸውን አክለው መግለፃቸውም ይታወቃል::

በዚህ የተነሳ እና በመክፈቻው ዕለትም እንዲገኙ ጥሪ ከተደረገላቸው የተለያዩ ዜጎች ብዛትና የጥንቅር ስፋት በመነጨ የሶስተኛው ፓርላማ ሁለተኛው ዘመን ይበልጥ ዴሞክራሲያዊ፣ ውጤታማና ስርዓት የሰፈነበት እንደሚሆን ብዙዎች ከወዲሁ ገምተዋል:: ይሁንና ተአማኒ ከሆኑ የቅርብ ምንጮች የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው ፓርላማው ውስጥ ወንበር በያዙ የተወሰኑ የቅንጅት ተመራጮች ተባባሪነት እና በክቡር ዶ/ር መረራ ጉዲና አስተባባሪነት ተጠንስሶ ለተግባር እንዲበቃ የታቀደ ተፃራሪ አጀንዳ ያለው እንቅስቃሴ መኖሩ ታውቋል::

ይኸው ዕቅድ ህገ ወጥ በሆነው የስደቱ ቅንጅት እና ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ በሚገኝ ተጠርጣሪ የቀድሞ አመራሮች ምስጢራዊ ተሳትፎ የተቀናበረና በዋናነት ዶ/ር መረራን ጨምሮ ሌሎች ሁለት ተቃዋሚ የፓርላማ ተመራጮች ተሳትፎ የሚመራ ነው:: በደረሰን መረጃ መሰረት ዋነኛ ዓላማውም የፓርላማውን የመክፈቻ ዕለት ጨምሮ በተከታታይ በቁጥጥር ስር የሚገኙት ተጠርጣሪዎች ይፈቱ በሚል መፈክር ከአጀንዳው እንዲወጣ አድርጎ በመወጠር ማወክ፣ ይህም ስርዓቱን አልተከተለም በሚል ዕድል

መነፈጉ ስለማይቀር እስከአሁን ለዚሁ ዓላማ ስምምነታቸውን የገለፁና ሌሎችንም በሂደት እንዲጨምር አድርጎ በማደራጀት ፓርላማውን ረግጦ መውጣት፤ አስከትሎም በዚሁ ዙሪያ ከአዳራሽ ወደ አደባባይ የሚወጣ ሁከት በማቀጣጠል በብጥብጥም ሆነ በሚፈጠር ውጥረት ግብን ማሳካት የሚሉትን እንደሚያካትት ለማወቅ ተችሏል።

በግንባር ቀደም አስተባባሪነት ክቡር ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ ክቡር አቶ ይልማ ታች፣ ክቡር አቶ ደርዛ ደዋኔ የተባሉ የቅንጅት ተመራጮች ሲገኙበት፤ ይህንኑ ዓላማ እስከ አሁን ተቀብለው ተባባሪ ከሆኑትም መካከል ክቡር አቶ ሽዋፈራ ይጥና፣ ማሙሸት ሰይፈ፣ ለገሰ ገ/ወልድ፣ እሸቴ ካሳሁን፣ የተከበሩ አቶ መላኩ ወርቅነህ፣ አቶ ይታየው ጥሩነህ እና የተከበሩ አቶ ለገሰ ቢራቱ የተባሉት የፓርላማው ተመራጭ የተቃዋሚ ወኪሎች እንደሚገኙበት ምንጮቻችን ያደረሱን መረጃ ያመለክታል።

ይህንኑ ዓላማ ተቀብለው በተጠቀሰው ዘዴ ለመተግበር ተሳትፎ እንዲያደርጉ የተጠየቁ አንጋፋ የተቃዋሚ መሪ የፓርላማ ተመራጮች እንደነበሩ የዜና ምንጮቻችን ጠቅሰው፤ እነዚህም የተከበሩ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ፣ የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ እና ክቡር አቶ ተመስገን ዘውዴ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ይሁንና ክቡር ዶ/ር በየነና አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ጥያቄውን ላቀረቡላቸው ወገኖች «እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ድርጅት ተገቢም ሆነ ጠቃሚ ነው ብለው እንደማያምኑና እንደማይቀበሉት» በመግለፅ ምላሽ ሰጥተዋል። በተመሳሳይ መልኩ ጥያቄው የቀረበላቸው አቶ ተመስገን ዘውዴም «የታቀደው ተግባርና የታለመው ግብ ያለንን ህጋዊነት ሊያሳጣና በህግም ሊያስጠይቀን ይችላል፣ በመሆኑም በጥንቃቄ ልናስብበት ይገባል» በማለት ምክር አዘል ምላሻቸውን እንደሰጡ ምንጮቻችን አስታውቀዋል።

ከዚህ ወጣ ባለ መልኩ ጭርሱኑ የዕቅዱ ሀሳብ ያልተነገራቸው፣ የተሳትፎ ጥያቄም ያልቀረበላቸው የተቃዋሚው ዋና መሪና የፓርላማው አባል የሆኑት የተከበሩ አቶ ልደቱ አያሌው መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። የእነ ክቡር ዶ/ር መረራ ቡድን አቶ ልደቱን አስመልክቶ የመረጠው ይህ አካሄድ አቶ ልደቱን እናማክር ወይስ ዝም እንበለው የሚል ጥያቄ በማንሳት «ከነገርነው አንድ ሊያጋልጠን፣ ሁለት በአደባባይ ሊቃወመን ይችላል» በማለት መሆኑን ምንጮቻችን አብራርተዋል።

በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡን አንድ ታዛቢ ምሁር «ዶ/ር መረራና ተባባሪዎቻቸው ያለሙት ጉዞ የትላንቱ የዶ/ር ነገደ ጎበዜ ምርጫውን መጠቀሚያ የማድረግ ስትራቴጂ ግልባጭ፣ የዚያ ሙከራ ውድቀትና ያስከተለው ፖለቲካዊ መደናበር የወለደው ሲሆን፣

የስደቱ ቅንጅት አመራሮችና ቃሊቲ የሚገኙ ተጠርጣሪዎች ሊሸከሙ የበቁትም መፈክሩ የእነሱን መፈታት ከፊት ለፊት ያደረገ በመሆኑ ብቻ ነው። ከመተማመንም ሆነ ከጋራ ራዕይ ግልፅነት የመነጨ አይደለም፤» በማለት ገልፀዋል። በማጠቃለልም «በዋናነት ወቅቱ በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው መስክ ሁከት ያላገደው መሻሻል የተመዘገበበት፣ በብዙ ዜጎች ዘንድም ቀጣይነቱ ትልቅ ተስፋ ያሳደረ በመሆኑ ብዙም የሚራመድ አይሆንም። ምናልባት የታቀደውን የፓርላማ የጨመረ ዴሞክራሲያዊ አሳታፊነት የሚሸራርፍ አሉታዊ ጣዕም ፈጥሮ የተፈጠረውን ቅርርብ ማሰናከል እንደ ሁለተኛ ድል የያዙ ከሆነም የገዢውም ሆነ ሌሎቹ የተቃዋሚ ወኪሎች ዛሬ ይህን ለማለፍ የሚያስችል ብስለት ላይ ናቸው ብዬ ስለማምን የሚሳካ አይሆንም።»